# ስለ አላነበብሁት የመደመር መጥሐፍ

መንግስቱ ሞሴ (ዶ/ር) ዳላስ

የጠቅላይ ሚኒስቴሩን መጽሐፍን አላየሁም ወይንም ላነብም አልችልም (ገና መውጣቱም ስለሆነ ማለት ነው) ግን መጽሐፉን ገምጋሚ የሆኑ የተመረጡት ተሳታፊወችን አዳመጥሁ። ከገምጋሚወች አቀራረብ እና የግምገማ አካሄድ ተነስቶ ግን ብዙ ሊታዩ የሚገባቸው ሀሳቦች ቢኖሩም በበኩሌ በዚህች አጭር ነቀፌታየ ተወስኛለሁ። በማነኛውም ጊዜ የማይታለፈው ግን የመጽሐፉ ደራሲ በአለፉት አራት አመታት በተግብር ተጉዞ ያሳየን ባህርያት እና “መደመር” የሚለው ጽንሰሀሳብ በእራሱ አገራችን እና ሕዝባችን ላሉበት አስከፊ ሁኔታ ፋይዳቢስ ብቻ አይደለም ተጨማሪ ዘረኝነትን የፍልስፍና ልባስ የሚያለብስ እና የጋራ እሴትን፣ ኢትዮጵያዊ ባህልን፤ ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ማንነትን፣ እና የትውልድ ትውልድ አንድነታችንን በልዩነት የሚተካ ብክለት እና በሐገራችን የተንሰራፋውን በህወሓት/ኦነግ ተረቀ ስራ ላይ የዋለውን ህገ መንግስት  መልክ የሚሰጥ ከምእራብ የተቀዳ ጽንሰሐሳብ ስለሆነ ግዜ በፈቀደ ወደፊት በተሻለ ለማሳየት ሁሉም ቢሰራ መልካም ይሆናል በሚል አሳስባለሁ።

ለማነኛውም ደራሲው (ጠ/ሚው) ሌሎችን ለመተቸት መጤ የፖለቲካ አስተሳሰብን ወደሐገራችን አምጥተው በሕዝብ እና ሐገር ላይ ጉዳት አደረሱ የሚል ተደጋጋሚ አስተያየት ሲሰጥ ቆይቷል። ከዚያም አልፎ ደረሳቸው በተባሉት መጽሐፍት እና ዛሬ ደግሞ በአዲሱ መጽሐፉ ያነን “የመጤ አይዲዮሎጅ” የሚለውን አሉባልታውን አጉልቶ ለማሳየት የመደመር ጽንሰሐሳብን ለተከታታይ ትውልዶች ስም ሰጦ የሱ ህልም እና ሐሳብ የተሻለነቱን ለማሳየትም እንደከጀለ ከገምጋሚወቹ ለመረዳት ችያለሁ (ድንቄም)። “አመድ በዱቄት ሳቀ” ይሏል አበው ሲተርቱ፤ ጠቅላዩ እና የፖለቲካ አይዲዮሎጅው ዘር እና የሐይማኖት ልዩነት ሲሆኑ ይህን እጅግ ኋላ ቀር ዘመን ያለፈበት ፖለቲካውን ኦሮሚያን ከሌሎች በማጽዳት ነጻ እና ሉአላዊ ሐገር ትሆናለች ብሎ በማሰብ ለአያሌ የአማራ ተወላጆች ሞት እና ስደት ፊታውራሪ መሆኑን ያለፉት አምስት የመከራ አመታት አሳይተውናል። መደመር የሚባለውም ጽንሰሐሳብ በኢትዮጵያ ውስጥ የኖሩት የተለያየ ቋንቋ ተናጋሪወች ሳይተዋወቁ፤ ሳይጋቡ፣ ሳይዋለዱ እንደኖሩ በማሰብ በልዩነታቸው ሆነው እንዲደመሩ ይሰብካል። እውነታው ግን ኢትዮጵያዊነት ከሁሉም ዘር መፈጠር ሆኖ ሳለ መደመር የዚሁ የዘር እና ሐይማኖት ተኮር እርዮተአለም ቅጣይ እና ማብራሪያ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። እናም መደመርን ድንቁርና የወለደው ወይንም ጭፍን ዘረኝነት የፈጠረው ባይሆን ኖሮ ለ3000 አመታት አብሮ የኖረ ውሕድ ሕዝብን እና ተወራራሽ የሆኑ ቤተእምነቶቹን ተለያይታችሁ ተደመሩ የሚል ሐሳብ ባላስፈለገው ነበር ወይንም ሐገርን አፍርሰን እንደገና በመደመር እንስራት የሚል አስተሳሰብ ባላስፈለገ ነበር። እናም ጽንሰ ሐሳቡ የምርጥ አሳቢ ምሁኡር ሳይሆን ቀሽም ዘረኛ ነው ብየ አልፈዋለሁ።

መደመር ከውሕድነት (Assimilation) የተለየ ሐሳብ ነው። አሜሪካኖች ከምስረታቸው እስከ 1920 ዊልሰን የሚባለው ፕሬዚዳንት እስከመጣበት ድረስ አገራቸውን ውሕድ ለማድረግ ሰርተዋል። ለዚያም ከአውሮፓ ከተለያዩ ሀገራት የፈለሱ ዜጎቻቸውን በማዋሀድ አንድ ባህል አንድ ቋንቋ እንዲወረሱ አበረታተው አሜሪካንን The land of Melting Pot በማድረጋቸው ዛሬ እኔ አይሪሽ ነኝ ቋንቋየ ይከበር፤ እኔ ፍሬንች ነኝ ፈረንሳይኛ ይነገርልኝ፤ ወይንም እኔ ጀርመን እና ፖሊሽ ነኝ የሚል ዜጋ የላቸውም። በእርግጥ ነው ጥቁር አፍሪካውያንን ስላገለሉ ጭቆናው እና የማሕበረሰብ ፍላሽ አሁንም አለ። ከ ፕሬዚዳንት ዊልሰን በኋ የተከተሉት የለዘብተኛ ፖለቲካ አይዲዮሎጅ (Liberalism) ተከታዮች የጥቁር ሕዝባቸውን ትግል ለማደብዘዝ እና ቀጥሎ የመጡት በተለይም The Neoliberals and Neocons ፖለቲካውን ከ ውህድነት እያወጡ Multiculturalism እንዲስፋፋ እያደረጉ ሲሆን ፖለቲካውን በማንነት ልዩነት ትኩረት እንዲኖረው በማድረግ ሁለቱ ተቃራኒ ፓርቲወች አንድ ፓርቲ ለሁለት ተከፍሎ የሚሰሩ እስኪመስል በዚህ አቋም አሳይተዋል። ለምሳሌ The Neoconservatives  የነጭ ዝርያ ደጋፊ  Neoliberals የአናሳ ማንነቶች ጠበቃ በመምሰል የቆየ የውህድ ፖለቲካቸውን

እያደበዘዙ በማንነት ፖለቲካ ለማህበራዊ ፖለቲካዊ ችግሮች መፍትሄነት እንዲሰጣቸው ተግተው ይሰራሉ። ይህ በሐገራቸው የሚሰሩበት የማንነት ፖለቲካ ከህገመንግስታቸው ውጭ እንጅ የተደገፈ እንዳልሆነ ግን ግልጽ ነው። የዚህ የማንነት ፖለቲካቸው ዝየዳ ሕዝብ ተበደልሁ ብሎ እንዳይነሳ የኢኮኖሚ እና ፖለቲካዊ ጥያቄወች በአንድ ሆኖ እንዳያቀርብ ወይንም ትኩረት እንዳይኖረው አደንዛዥ ስልታቸው ነው። ይህን የተማሩት በ 1960 ወቹ የሲቪል ነጻነት ተጋድሎ ነጭ ጥቁር፣ ቢጫ ጠይም ሳይል ስለታገላቸው እና ዳግመኛ ተመሳሳይ አይነት ኑሮ እና የመደብ ጀርባ ያላቸው ጥቁሮች - ነጮች እና ሌሎች ዜጎች በአንድ ቆመው የስርአት ለውጥን ለመጠየቅ እንዳይበቁ ለማድረግ ታስቦ የተሰራ እርኩስ እና ኢምፔሪያሊስት ተንኮን ነው።

ወደ ትናንቱ የመደመር ግምገማ ስንመለስ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ የመደመር ፍልስፍና ምንጭ እርሱ እንደሆነ ለማሳየት ይሞክር እና የያን ትውልድ ፖለቲካ ግን መጤ ሲል ይደመጣል። ከላይ በትንሹ እንዳሳየሁት መደመር ከአሜሪካ የአዲሱ ለዘብተኛ እና አዲሱ ወግ አጥባቂ አስተሳሰብ የተወሰደ መሆኑን ለሌላው ማሳያ የአሜሪካ የአሁናዊ ለዘብተኞች አስተሳሰብ በዘር፣ በጾታ፤ በገቢ፤ በቋንቋ እና ባህል ላይ የተመሰረተ Multiculturalism በሚባል አዲስ አስተሳሰብ እየሰሩበት መሆኑ እና ለእነሱም ሰፊ የተቃውሞ ትግል እንዳለ ለማሳየት እወዳለሁ። ይህ Multiculturalism የተለያዩ ባህሎች ተደምረው ይኖራሉ እንደማለት ሲሆን አዲሱ የአሜሪካ የግራ ኃይል (ማርክሳውያን) እና ክላሲክ ወግ አጣባቂወች በጽኑ ይቃወሙታል። ሌላው የ Multiculturalism የአሜሪካንን ሕዝብ ጥቁር፤ ነጭ፤ ጠይም፡ ወይም ላቲኖ፤ እስያዊ አለያም በጾታ ደግሞ ወንድ፤ ሴት፣ ወንድም ሴትም ያልሆነ፤ ወዘተ እያለ የሚከፋፍል በመሆኑ እና የሕዝቡን የቆየ ወግ እና ልማድ ያጠፋ በይበልጥም ውህድነት (Cultural and ethnic assimilation) እንዳይቀጥል እንቅፋት የሆነ በመሆኑ ነው።

ይህ አዲሱ የአሜሪካ ሁለት ፓርቲወች አስተሳሰብ (ሁለቱም ፓርቲወች በለዘብተኞች የተያዙ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ) የተሰራችበትን ቢያንስ በአውሮፓ መጤወች Melting-Pot ወይም ውህድነትን (Assimilation) ስለማይቀበሉ ከሁለቱም ፓርቲወች በሁለቱም ፓርቲወች የወግ አጥባቂው ክፍሎች ጭምር ተቃዋሞ እየተነሳበት ሲሆን በይበልጥ የሀይማኖት አባቶች እና ልጆቻቸውን በስርአት የሚያሳድጉ ወላጆች ያወግዙታል። ሌላው የክላሲካል ወግ አጥባቂ እና የአሜሪካ ግራ ፖለቲካ እምነት ተከታዮች ይህን የለዘብተኞች የፖለቲካ ቁማር ከፋፋይ በሚል ይፈርጀዋል። ባጭሩ መደመር አዲስ ፈጠራ ሳይሆን ከዚህ ከአሜሪካን ለዘብተኞች (Multiculturalism) የተቀዳ መጤ አስተሳሰብ ነው። ጠቅላይ ሚኒስቴሩ እና የዘር ፖለቲከኞችን በስም ይደግፉ እንድንል መልካም ገጽታ ለመስጠት ከውጭ የተቀዳ አስተሳሰብን እየቀነሱ መደመር ብለው አሳምረው በተደጋጋሚ መጽሀፍ ደርተውልናል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ወግዱ እያላቸው መሆኑን እና መደመር ብለው ያሳዩንን ቤተ እምነትን የመከፋፈል፤ ሕዝብን በቋንቋ እና ኃይማኖት መለያየት ጽንሰሀሳብን የጠላት ቅጅ መሆኑን ሰው እንዲነግረው ወይንም ለከንቱ ውዳሴ የተሰለፉ አድርባዮች ገጽ እንዲሰጡለት አይፈልግም።

እውነታው እኛ ኢትዮጵያውያን ውህድ ነን። በአማራ ውስጥ ኦሮሞነት አለ። በትግሬ ውስጥ አማራነት አለ ወይንም የተገላቢጦሹ ማለት ነው። ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው የገዥወቻችን (ነገሥታቱ) የዘር ማንነት ከሁሉም የተዛነቀ በመሆኑ እሩቅ ሳንሄድ ጠባብ ብሔርተኞች አምርረው የሚጠሏቸው አፄ ሚኒሊክን እና እቴጌ ጣይቱን ማየት በቂ ምሳሌ ሊሆንልን ይችላል። እናም የጠቅላዩ አስተሳሰብ አንድም ከውጭ ከአሜሪካኖች አስተሳሰብ የተቀዳ። ሌላም ዘረኝነትን ለማስቀጠል የተዘየደ ፋይዳቢስ ድሪቶ ማለት ይቻላል።

ይህን ካልሁ በሁአላ ስለመጽሐፍ ምረቃው እና ገምጋሚወቹ አጭር አስተያየት ልስጥ። መጽሐፉን ስለአላነበብሁት መጽሐፉን የመተቸች ብቃት የለኝም። ሆኖም ከላይ እንዳልሁት መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ ከመሆን እንደማይዘል ግን ከእርሱ መነሳት በቂ ግንዛቢ ሰጭ ይመስለኛል።

የመጀመሪያው ገምጋሚ ደበበ እሸቱ መልካም አድርጎ እና ሐሳቦቹን በውብ ቋንቋ ሰድሮ ተጠንቅቆም መስመር ሳያልፍ ግመገማውን ከውዳሴ ጋር ዘንቆ አቅርቦታል። ከሁሉም በላይ ግን የደበበ እሸቱ ግምገማ ከተከታይ ገምጋሚዎች የተሻለ ሆኖ አግኝቸዋለሁ።

እኔ የመጽሐፍ ግምገማ አይደለም ያደረግሁ ስላላነበብሁትም መገምገም አልችልም ግን ከሰማሁት እና ከገምጋሚወቹ የመደመር ትውልድ ግምገማ በህይወት ተፈራ የቀረበው የመጽሐፉን በህልመኛው ትውልድ ላይ ካሰፈረው አስተያየት እና ነቀፌታ አንጻር ገመገሞች ለማለት አያስደፍርም። ከከንቱ ውዳሴ ወጥታ ሕልመኛው ትውልድ (ያትውልድ) የመጣበትን የዘመን አገራዊ እና አለማቀፋዊ  ነባሪ ሁኔታ ማሳየት ብትሞክር ኖሮ የዚህን የመደመር ቆሻሻ የዘር ተዘር ልዩነት እና ጥላቻ መርህን አጥፊነት ባስተማረች ነበር። ብሎም ትውልዱ (ያትውልድ) ለነበረው አገራዊ እና አለማቀፋዊ ነባሪ ሁኔታ እና ያቀረበውን መፍትሄ ሀሳብ ለምሳሌ የአውሮፓ ቅኝ አገዛዝ ገና በአፍሪካ እንደተንሰራፋ መሆን እና አሜሪካ የዚህ ቅኝ ገዥ አጋር መሆኗ አንዱ ሲሆን ይህን ለመታገል ከሌላው ጎራ ቅኝ ግዛትን እየታገሉ ከነበሩት እነ ቬትናል፤ ቻይና የተከተሉትን እርዮታለማዊ ሞዴል ለመከተል ሞክሯል። የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምም አውግዟል። በሐገራዊ ሁኔታም ተንቀሳቅሶ ትውልዱ ቀላል የማይባል ለውጥም ለማሳየት ታግሏል። እንደዋና ማታገያ ግንባር ቀደም መፈክር የነበረው የመሬት የመሬት ላራሹ መፈክር እና ለዚያ እውን መሆን የተደረገው ትግል ቢያንስ ገባርነትን አስወግዷል።-

የመደመር ትውልድን መጸሐፍ አቅራቢ ያንን ታጋይ ትውልድ ምንም እንዳልሰራ እና እንዴውም እርባና የለሽ በሁለት ቃላት ልዩነት እንደተጋደለ በቆመበት መድረክ ሁሉ "በ ቸ እና ሸ" ተለያይተው ከመኖር ወዳለመኖር እንዳጠፉ በማለት ለያትውልድ ያለውን ጥላቻ በተደጋጋሚ አሳይቷል። በዚህም መጽሐፉ ያነኑ ድሪቶውን መድገሙን “መሐመድ ሐሰን” ገልጾታል። በነገርችን ላይ መሐመድ ሐሰን ማለት የያትውልድ ሰው ቢሆንም እድሜውን እና እውቀቱን በሰፊው የሰጠው በማንነት ታሪክ ሥራ እንጅ ለሉአላዊት ሐገር አድ ሆና መቀጠልም አይደለም። ሆኖም ህይወት ተፈራ ግን የምታውቀውን አገር አቀፍ ሁኔታወች ትውልዱ የከፈለውን ዋጋ  እና በኢትዮጵያ ታሪክ ያለውን ሁነኛ ድርሻ ከማሳየት ይልቅ በዘረኞች የተሰጣትን መድረክ በከንቱ ውዳሴ አሳልፋዋለች።

ደበበ እሸቱ የሄደበት እና ያሳየው የትውልዱን ጥንካሬወች እና መጽሐፉን ከእራሱ ትውልድ ጋር በማነጻጸር ለወግ አጥባቂ ለተባለው ግን አርበኛ ትውልድ መልካም ስራወቹን በተገቢ ሰድሮ ተችቷል። ለምሳሌ የመንግስቱ ለማን፤ የጸጋየ ገ/መድህንን፤ የአፈወርቅ ተክሌን ወዘተ እና የነበራቸውን እጅግ ዘመናዊ አስተሳሰቦች በማሳየት መጽሀፉ ከስም አሰጣጥ ጀምሮ ሊያሳይ ያለመውን ሀሳብ አምክኗል ብል ስህተት አይሆንም። ለማነኛውም ሕይወት ተፈራ ያትውልድን "በ ቸ እና በ ሸ" ሳይሆን መሰረታዊ የለውጥ አውዶች ልዩነት ላይ ገፈት ቀማሽ መሆኑን ባለማሳየቷ እጅግ አፍሬባታለሁ ብሎም ለከንቱ ውዳሴ እዚያ በመገኘቷ አዝኛለሁ። ለምሳሌ የዴሞክራሲ ጥያቄ ጎልቶ የወጣበት የግዜ ስሌዳ በዚያ ትውልድ ደም ብራና ስር መሆኑን እንዴት ሊዘለል ይቻላል? ሰድቦ ለሰዳቢ እንዲሉ መሐመድ ሐሰንም እርሷ ያቀበለችውን ለበቅ እና መጽሀፉ ሊያሳይ ያሰበውን የዚያን ትውልድ የማጠልሸት ሐሳብ ለአካለመጠን አድርሶ እርሱም ለተጨማሪ ከንቱ ውዳሴው ጠቅላዩን እና እዚህ ግባ የማይባል ሀሳቡን የራስ ዳሽንን ያክል የገዘፈ ለማድረግ አንጠራርቶታል። "ግዚያዊ ሕዝባዊ መንግስት" ስንል እነሱ " በኋላ ከቀረጠፋቸው "ከግዚያዊ ወታደራዊ ደርግ ጋር ወደፊት" ብለው የነጻ እርምጃ ጋሻ ጃግሬወች በመሆን አያሌ የህልመኛውን ትውልድ አባላት አሳርደዋል። "ዴሞክራሲ ያለገደብ" ስንል "ዴሞክራሲ በገደብ"ብለው ጎራ ለይተው እና ሕዝባችን ለነጻነት ብቁ አይደለም ብለው በያደባባዮች ለመብት መከበር የተሰለፉ አርሶ አደሮች፤ ላባደሮ፤ ተማሪ አስተማሪወችን አስረሽነዋል። እና ያ በ ቸ እና ሸ የነበር ልዩነት ሳይሆን አሁንም ለ50 አመታት ያልተመለሰ ፋና ወጊ ጥያቄ ነበር በመጽሐፉ ከወፍ ላባ የቀለለ ሆኖ የቀረበው። እናም  ህይወትን ያክል የትውልድ አባል እንዴት የትውልዱን ማንነት ሲዳጥ አንድ ነገር ሳይወጣት በከንቱ ውዳሴ ለተሳዳቢው አምድ ተጨማሪ ሰጥታ ትወርዳለች? አበስኩ ገበርሁ!!!